የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ቀን 12 መስከረም 2008
Date
ቁጥር መ/190-8/3/1
Ref. No.

ለትምህርት ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

መስሪያ ቤታችሁ ግንቦት 6 ቀን 2006 ዓ.ም በቁጥር 7/1-9214/641/35 በጻፈው ደብዳቤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቴክኒካል ረዳቶች የሙያ ዕድገት መሰላል/Carear Structure/ ለረዥም ጊዜ ሳይሻሻል የቆየ በመሆኑ ልምድ ያላቸውን ሰራተኞች በሥራ ላይ ለማቆየት አዳጋች መሆኑን ገልጾ የቴክኒካል አሲስታንት የዕድገት መሰላል ፕሮፖዛል በማዘጋጀት የላከ ሲሆን ማሻሻያው ታይቶ እንዲጸድቅለት ጠይቋል፡፡

በጉዳዩ ላይ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተያየቱን እንዲሰጥበት ተጠይቆ ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ8/ ጠ10/10/265 በጻፈው ደብዳቤ በሰጠው ምላሽ የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቴክኒካል ረዳቶች የሙያ ዕድገት መሰላል/Carear Structure/ ማሻሻል ያስፈለገው በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች ላይ ያተኮረው የከፍተኛ ትምህርት ሰፊ የተግባር ትምህርትን የሚያካትት መሆኑን ጠቅሶ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሳይንሳዊ መሣሪያዎች እየረቀቁ መምጣት ከቀድሞው የተሻለ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ለሥራው አስፈላጊ መሆናቸውን አብራርቶ በቀረበው ጥያቄ ላይ አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ አቅርቧል፡፡

በመሆኑም ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ከግምት በማስገባት የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አሻሽሎ ያቀረበው የደመወዝ ስኬልና የተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ በስራ ላይ እንዲውል የተፈቀደ መሆኑን እየገለጽን ለአፈጻጸም ይረዳ ዘንድ ሚኒስቴሩ ያቀረበውን ሠነድ አያይዘን መላካችን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር
ደብረ አበራ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
- ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

ስልክ 011-1-22-67-67 Tel.
ፋክስ 22 62 92 Fax
ፖ.ሣ.ቁ 1268 P.O.Box
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia

